# ስለየአዲሲቱ ኢትዮጵያ መስራች አባት መለስ ዜናዊ ምንተበሎ ነበር?

## ክፍል አንድ

አዲስ ቶልቻ

08-19-14

የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መስራች አባት (founding father) የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር መለስ ዜናዊን ዜና ዕረፍት የሰማነው ልክ የዛሬ ሁለት ዓመት ነሃሴ 15፣ 2006 ዓ/ም ነበር። ይህን ተከትሎ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ሕጻናትና አዋቂዎች ፣ አረጋውያን፣ የመንግስትና የግል ሰራተኞች፣ አርሶና አርብቶ አደሩ፣ ባለሃብቱ፣ ምሁራንና የኀዳና ተዳዳሪዎች፣ ስራፈላጊዎች ... ሁሉም በየፈርጁ በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ወድቀው ነበር፡፡ በኢተዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የሃዘን ድባብ አጥልቶም ነበር።

ይህ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በጥልቅ የሃዘን ስሜት ዕንዲዋጥ ያደረገ አስደንጋጭ ሁኔታ መንስኤው አንድና እንድ ነበር፡፡ የቀደሞው ጠቅላይ ምኒስትር መለስ ዜናዊ ከወጣትነት እድሜያቸው ጀምረው ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለዘመናት የተጫነውን አስከፊ ድሕነትና ይህ ድህነት ያስከተለውን አስከፊ የአገር ገፅታ ለመለወጥ በሰሩት አኩሪ ስራ በእያንዳንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ጉልህ ስፍራ በመያዛቸውና ተገቢውን አክብሮት በማግኘታቸው ነው፡፡

ይህ ከዕውነተኛ ልባዊ የህዝብ ፍቅር የመነጨ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ተግባርና ራዕይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ሕይወት ወደተሻለ ደረጃ አሸጋግሯል፡፡ በቀጣይነትም የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ሕይወት ወደተሻለ ደረጃ ያሸጋግራል የሚል ተጨባጭ ተስፋ ፈንጥቋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሻራ በቀጥታ ያረፈባቸው ውጤቶችና ተስፋዎች፣ እንዲሁም ኢትዮጵያዊው መለስ ዜናዊ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ሕዝቦችን ከድሕነት ማላቀቅ በሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና ሰላምን ማስፈን በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ያቀረቡዋቸው ድንቅ ምሁራዊ ትንታኔዎች ስምዋ በመጥፎ ሲነሳ የቆየችውን ኢትዮጵያንና አፍሪካን ገፅታዋን በበጎ በመለወጥ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ታዲያ የዛሬ ሁለት ዓመት የእነዚህ ሁሉ ስኬቶች መሃንዲስ የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ድንገት ከዚህ ዓለም በሞት መለየት፣ በበጎ ምግባራቸው የሕዝቡ ልብ ውስጥ ዘልቀው የገቡትን ያህል ሃዘኑም በህዝቡ ልብ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ነበር፡፡ ህዝቡም በገጠመው መሪር ሃዘን በነቂስ ወጥቶ በዕንባ ተራጨ ፡፡ ህዝቡ በወቅቱ ተሰምቶት የነበረውን ጥልቅ ሃዘን በለቅሶ ብቻ አልነበረም የገለፀው።

የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መስራች አባት የጀመሯቸውን ስራዎች ለማስቀጠል፣ ራዕያቸውንም ለመፈፀም ቃል ገብቶ ነበር፡፡ ተተኪ መሪዎቹም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ራዕይ ለማሳካት ጠንክረው እንዲሰሩ አሳስቦ ቃል አስገብቶ እንደነበረም እናስታውሳለን፡፡ በዚህ አኳኋን ራዕያቸውንና ዕቅዳቸውን በማሳካት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሕያውነት ለማረጋገጥ በጋራ ሃገራዊ መግባባት ላይ ደርሶ ነበር፡፡

ለሕዝብ አሳቢ፣ ብልህና ቆራጥ የሆኑት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሕልፈተ ህይወት የኢትዮጵያዊያን ሀዘን ብቻ አይደለም፡፡ ሕዝብን ከድህነት ማላቀቂያ ራዕያቸውን የተጋሩ፣ አስተዋይ አዕምሯቸው ባፈለቀው ሃሳብ የሰፈነውን ሰላም የተቋደሱና የሰላም ተስፋ ያደረባቸው፣ እነዲሁም የአፍሪካን ፍላጎትና ጥቅም ለማስጠበቅ በጠበቃነት የወከሏቸውና የስራ ፍሬያቸውን ይጠብቁ የነበሩ አፍሪካውያን ሁሉ ጥልቅ ሃዘን ገብቷቸው ነበር፡፡

በዚህ መነሻነት የአፍሪካና የተቀረው ዓለም መሪዎች የሃዘን ስሜታቸውን ገልፀው እንደነበረም ይታወሳል፡፡ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃንም ስለ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በስፋት ዘግበው ነበር፡፡ ዛሬ የኢተዮጵያ መስራች አባት መለስ ዜናዊ ሁለተኛ ሙት ዓመት ስንዘክር ታላቅነታቸውና ክብራቸው የተገለፀባቸውን ህልፈተ ህየወታቸውን ተከትሎ የተሰጡ አስተያየቶቸ ሁለት ዓመት ወደኋላ ተመልሼ ማስታወስ አስፈላጊ ሆኖ

አግኝቼዋለሁ፡፡ በአጋጣሚ በእጂ ገበተው የነበሩትን ታስታውሏቸው ዘንድ በቀጥታ ተርጉሜ እንደሚከተለው አቅርቤያቸዋለሁ።

## ጃኮብ ዙማ፣ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት

ለአፍሪካና ለኢትዮጲያ ህዝብ በአህጉራዊና በአለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ንቁ መሪ የነበሩትንና የተለየ ብቃት ያላቸውን መሪ ማጣት እጅግ አሳዛኝ ነው። መለስ ዜናዊ ለአገራቸው ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ጭምር ጠንካራ መሪ ነበሩ። በተለይ የአፍሪካ ቀንድን በመወከል በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ላይ መቅረባቸው የታወሳል።

## ኤለን ጆንሰን፣ የላይቤሪያ ፕሬዚዳንት

መለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ ለውጥ መሪና የአህጉሪቱ ግንባር ቀደም ምሁር ነበሩ። በአካባቢያዊ ስብሰባዎች ላይ ከአፍሪካ እደገት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ የተለየ ምሁራዊ አቅምና ብቃት ያላቸው በመሆናቸው ቀዳሚ ነበሩ።

የመለስ ሞት የሚያስከትለወ የስልጣን ሽግግር ላይ ችግር ይፈጠራል የሚል ስጋት የለኝም። ኢትዮጲያ ውስጥ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ዕውን ለማድረግና ነፃ ማህብረሰብ ለመመስረት የአካባቢውን መሪዎች ድጋፍ የሚያገኙ በርካታ መሪዎች አሉ፡፡

## ባርናባ ቤንጃሚን፣ የደቡብ ሱዳን የማስታወቂያ ሚኒስትር

ለደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ ህዝብና ለምስራቅ አፍሪካ አካባቢ እጅግ በጣም አሳዛኝ ቀን ነው። መለስ ታላቅ መሪ ነበሩ፡፡ በአጎራባች አገራት መካከል ሰላም እንዲሰፍን ሁሌም ተግተው የሚሰሩ መሪ ነበሩ።

እኛ በደቡብ ሱዳን የምንኖር በተለይ ኢትዮጵያንና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ምንጊዜም ወዳጃቸውን የማይከዱ በመሆናቸው እንደ አጋራችን እናስባቸዋለን። በመሆኑም በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት አዝነናል።

## ጆስ ማኑኤል ባሮሶ፣ የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት

መለስ ዜናዊ የተከበሩ የአፍሪካ መሪ ነበሩ። ለአመታት ከራሳቸው አገር ህዝብ በተጨማሪ በአጠቃላይ የአፍሪካን ህዝብ ኑሩ ለማሻሻል በአፍሪካ ህብረት፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በልማት፣ በሰላምና መረጋጋት ዙሪያ በመስራት በተለይ በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያረጋገጡ መሪ ነበሩ።

ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ስርአት መዳበር፣ ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለህዝብ ብልፅግና እንዲሁም ለሌሎች ለአካባቢው አገራት መረጋጋትና ትስስርን የጀመረችውን ስራ አጠናክራ እንደምትቀጥል እተማመናለሁ።

## ዴቪድ ካሜሮን፣ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒሰትር

መለስ ዜናዊ በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ የአፍሪካ ልሳን የነበሩ፣ እንዲሁም ለሱማሊያና ሱዳን የአመራር ክህሎትና ራዕይ የለገሱ መሪ ነበሩ። ለኢትዮጵያ ልማት በተለይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጲያውያንን ከድህነት በማውጣት ለአገራቸው ያበረከቱት አስተዋጽኦ ለአካባቢው ተምሳሌት ሆኗል።

መለስን አጥተናቸዋል። ከቤተሰቦቻቸውና ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በሃሳብ አብረን ነን።

## ቶኒ ብሌር፣ የቀድሞ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር

የመለስ ዜናዊን ህልፈት የሰማሁት በታላቅ ሃዘን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በተለይ አገራቸውን ከአስከፊ ድህነት ወደ ኢኮኖሚ እድገትና ልማት እንዲሸጋገር በመምራታቸው

በኢትዮጲያ ታሪክ ውስጥ የጎላ ስፍራ ያላቸው መሪ ናቸው። ለቤተሰባቸውና ለኢትዮጲያ ህዝብ መፅናናትን እመኛለሁ።

## ባራክ ኦባማ፣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት

የመለስ ዜናዊን ሞት የሰማሁት በከፍተኛ ሃዘን ነው ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ እደገት፣ በተለይ ድሆች ኢትዮጲያዊያንን ከድህነት ለማውጣት ባላቸው ብርቱ ተነሳሽነት ዕውቅና ሊሰጣቸው ይገባል። ከመለስ ዜናዊ ጋር የተገናኘሁት በግንቦት ወር 2004 ዓ/ም በተካሄደው የጂ-8 አገራት ስብሰባ ላይ ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጲያውያንን በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከድህነት ለማውጣት ባላቸው ፍላጎት በግሌ ያለኝን አድናቆት ገልጬላቸው ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ ሰላምና ደህንነት ላበረከቱት አገልገሎት፣ ለአፍሪካ ህብረት ላበረከቱት አስተዋፅኦ፣ አፍሪካን በመወከል በዓለም አቀፍ መድረኮች ላሰሙት ድምፅ ታላቅ አክብሮት አለኝ።

መለስን ያለጊዜው በማጣታችን በአሜሪካ ህዝብ ስም ለቤተሰቦቻቸውና ለኢትዮጲያ ህዝብ መፅናናትን እየተመኘሁ፣ የአሜሪካ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ወዳጅነት ለማስቀጠል ያለውን ቁርጠኝነት አረጋግጣለሁ።

የኢትዮጵያ መንግስት ለልማት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለአካባቢያዊ ሰላምና መረጋጋት፣ ለሰብአዊ መብት መከበርና ለህዝብ ብልፅግና የሚያደርገውን ጥረት እናበረታታለን።

## ሱሳን ራይስ በአሜሪካ የውጭ ጉዳየ መስሪያ ቤት የአፍሪካ ተጠሪ የነበሩ

ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ድንቅ ነገሮች ቀዳሚው ወደር የለሹ ብቃታቸው ነው፡፡ የዕድሜ ልክ ተማሪ ናቸው፤ ራሳቸውንና ሌሎችንም አስተምረዋል፡፡ መለስ፣ ልበ ብርሃን

ብቻ አልነበሩም፤ የማይንበረከኩ ብርቱ ተከራካሪ ብቻ አልነበሩም፡፡ እውቀት የተጠሙ ብቻም አልነበሩም፡፡ ባልተለመደ ሁኔታ ብልህ፣ ሌሎች ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተፅዕኖዎች በሚያሳድሩባቸው አጋጣሚዎች እንኳን የነገሮች አዝማሚያ ምን እንደሚመስል መገንዘብ የሚችሉ የተለየ ብስለት የነበራቸው ነበሩ፡፡

እንደ ሁለት መንግስታት ተወካዮች፣ እንደጓደኛሞችም አንዳንድ ግዜ ሰፊ የአቋም ልዩነቶች ኖረውን የማንግባባባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በኢኮኖሚክስ፣ በዴሞክራሲ፣ በሰብአዊ መብት፣ በአካባቢያዊ ደህንነት ወይም በየአገራችን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ በምንከራከርበት ወቅት ሁለት የሚያስደንቁ ባህሪያት አይቼባቸዋለሁ፡፡ የመጀመሪያው መለስ በእያንዳንዱ አቋሚቸው ላይ ምክንያታዊ መሆናቸውና ውሳኔ አሰጣጣቸውም ጥንቃቄ የተሞላበት መሆኑ ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ ከርዕዮተ አለም ይልቅ ለሚወዱት አገራቸው ባላቸው የመፃኢ ግዜ መልካም ራዕይ የሚመሩ መሆናቸው ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ስኬት ላይ ለመድረስ ቁርጠኛ ነበሩ፡፡ ይህ ቁርጠኝነታቸው የግል ሕይወታቸውን አይመለከትም፡፡ መለስ የኢትዮጵያ ልጅ የሆኑትን ያህል የአዲሲቱ ኢትዮጵያ አባት ናቸው፡፡ በኢትዮጵያዊነታቸው ጥልቅ ኩራት የሚሰማቸው መለስ፣ ኢትዮጵያውያን የድህነት ታሪካቸውን፣ ረሃብና እርስብርስ ያላቸውን ልዩነት እንዲያሸንፉ ለማስቻል ቁርጠኛ ነበሩ፡፡

መለስ በ1980ዎቹ ረሃብ የረገፉ ለጋ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ውስጣቸው ቀርተዋል፡፡ያ ወቅት ያሳደረባቸው አስከፊ ስሜት ኢትዮጵያን የስቃይ ሜዳ እንድትሆን ያደረጋትን አምባገነን ለማስወገድ እንዲነሱ አድርጓቸዋል፡፡ አጥብቀው የሚመኙትን በአገር ደረጃም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ቀጣይነት ያለው እድገት ለማስመዝገብ አነሳስቷቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያውያን ያላችሁ የሰላም ፍላጎትና በአለም ዓቀፍ መድረክ ልታበረክቱት የምትፈልጉት በጎ አስተዋፅኦ እንዲታወቅ ለማድረግም አነሳስቷቸዋል፡፡

የመለስ ራዕይና ተፅእኖ በኢትዮጵያ ድንበር የተወሰነ አልነበረም፡፡ በመላው አፍሪካ የሚገኙ መሪዎች የሰላም ጉዳዮችንና የኢኮኖሚ መሻሻል በሚያሳዩባቸው ጉዳዮች ላይ ያማከሩዋቸው ዘንድ ይፈልጓቸው ነበር፡፡ የአፍሪካ ሕብረት ምስረታ ዕውን እነዲሆን

አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ኢጋድ እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡ ሽብርተኝነትን ፊት ለፊት ከመጋፈጣቸውም በላይ ሊገነቧት በመጣር ላይ የሚገኙትን አገራቸውንና አካባቢውን ለማዳከም የሚንቀሳቀሱ ፅንፈኛ ጦረኞችን ተዋግተዋል፡፡

## ባን ኪሙን፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ

መለስ ዜናዊ በተለየ የአመራር ብቃታቸው የአፍሪካን ጉዳይ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማከናወን እንዲሁም ባስመዘገቡት የኢኮኖሚ እድገት የሚታወሱ ታላቅ መሪ ናቸው፡፡

## ኦሊሴንጎን ኦባሳንጆ፣ የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዝዳንት

የመለስ ዜናዊ ሞት አፍሪካ ደፋርና ባለራዕይ መሪ የተነጠቀች ያህል የሚቆጠር ነው፡፡ የኢትዮጵያው መሪ መለስ ዜናዊ ሞት አፍሪካን ቁርጠኛ፣ ሩቅ አሳቢ፣ ባለራዕይና ደፋር መሪ አሳጥቷታል፡፡

መለስ በዛሬይቱ አፍሪካ አንፀባራቂ ከሆኑት መሪዎች አንዱ ነበሩ፡፡ በአፍሪካ ሕብረት ያሳዩትን ስኬታማ ስራ አስተውያለሁ፡፡ መለስ ብልህ በመሆናቸው የአፍሪካ መሪዎች እኔም ጭምር የአፍሪካ ህብረትንና የኔፓድን ፕሮግራም እንዲያዘጋጁ ወስነን ሰጥተናቸው ነበር፡፡ ሞታቸው በጣም አስደንጋጭ ዜና ነው የሆነብኝ፡፡

**ይቀጥላል**